Any claim arising out of a contract of insurance shall be barred after two years from the occurrence giving rise to the claim or from the day when the parties knew of the occurrence. በሚል ተቀምጧል፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሰረት በኢንሹራንስ ውል ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ ጥያቄውን ለማቅረብ የሚያስችለው ምክንያት በተከሰተ ወይም ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳዩን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመድን አረቦን መከፈል የነበረበት ጊዜ ሁለት ዓመት ያለፈው ስለመሆኑ ተጠሪም የማይክደው ፍሬ ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ አጥብቆ የሚከራከረው ለጉዳዩ

አግባብነት ያለው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ የተመለከተው ሳይሆን በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1845 ስር የተመለከተው ነው በማለት ነው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ የኢንሹራንስ ውልን መሰረት ያደረገ እንደመሆኑ መጠን በንግድ ሕጉ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የማይኖርበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ከላይ የተመለከተው ድንጋጌ ግልጽ ከመሆኑ አንፃር የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው ድንጋጌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 754/1/ ስር የተመለከተው ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677 እና 1845 መሰረት በማድረግ አመልካች ያቀረበውን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረገው ያላግባብ ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 102951 ጥቅምት 05 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 72894 ግንቦት 03 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቀው የመድን አረቦን ይከፈለኝ ጥያቄ በሁለት አመት ይርጋ ጊዜ የታገደ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 46808

ሚያዝያ 06 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ/ማ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ጫልቱ ሚደግሳ - በሌሉበት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመድን ሰጪ የኃላፊነት መጠን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሰሌዳ ቁ 3ኦሮ 03004 የሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ንብረትነቱ የአቶ ሐብታሙ አለነህ ሆኖ በአቶ ጌታነህ አለነህ ሲሽከረከር የሰሌዳ ቁጥር 3 ኢት 16818 የሆነ መኪና ገጭቶ በመኪናው ውስጥ የነበሩ አቶ ተመስገን ሚደግሳ እና ወ/ሮ ስኳሬ ዲቲን የገደለ በመሆኑ የካሣ ጥያቄ ክስ በወራሾች ቀርቦ አመልካችም በመድን ውል መነሻ በክርክሩ እንዲገባ መደረጉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የአሁን አመልካች ኃላፊነት እና የካሣ መጠንን አስመልክቶ ክርክር ያቀረበ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው የኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከሳሾች ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ካለ በኋላ የካሣ መጠኑም ብር 106,400(አንድ መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ) ብር እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካሳ መጠኑን በማሻሻል ባጠቃላይ ብር 68,200(ስልሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፈል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ሲል ሰኔ 16/2001 ዓ.ም በጠበቃው አማካይነት ባቀረበው አቤቱታ የሟች ወራሾች በቀጥታ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፣ የካሳ መጠን አስመልክቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስሕተት እንደሆነ እና ካሣ መከፈል አለበት ከተባለም የአመልካች የኃላፊነት ወሰን ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ለአንድ ሰው እንደመሆኑ በጠቅላላ ከስልሳ ሺህ(60,000) በላይ የሚከፍልበት አግባብ ባለመኖሩ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በዚህ ረገድ እንዲታረም ሲል አመልክቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ከመረመረ በኋላ የአመልካች የኃላፊነት ወሰን ከብር 60,000(ስልሳ ሺህ) በላይ መወሰኑ በአግባቡ ስለመሆኑ ለመመርመር ተጠሪ እንዲቀርቡ አዝዟል፡፡ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲወሰን ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ አገናዝበን መርምረናል፡፡

የአመልካች ኃላፊነት የመነጨው ከመድን ውል ስለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ አመልካች ለሥር ተከሳሽ የሰጠው የመድን ሽፋን የሦስተኛ ወገን ኃላፊነት ስለመሆኑ እና ለአንድ ሰው የሚከፈለው ካሣ መጠን ጣሪያው ብር 30,000(ሰላሳ ሺህ) ስለመሆኑም አላከራከረም፡፡ አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው የሥር ተከሳሽ መኪና ጉዳት ያደረሰው በሁለት ሰዎች ላይ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡

ስለሆነም በውሉ መሠረት የአመልካች ኃላፊነት ወሰን ብር 60,000(ስልሳ ሺህ) መሆኑ ታውቋል፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 665(2) መሠረት ደግሞ የመድን ሰጪው ኃላፊነት በመድን ውሉ የተመለከተውን የገንዘብ ወሰን መሠረት ካሣ መክፈል ግዴታ አለበት፡፡ አመልካችም እየተከራከረ የነበረው የኃላፊነት መጠን በውል ከተወሰነው በላይ ሊሆን እንደማይገባ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በግልፅ ውሉን እና ሕጉን መሠረት አድርጐ ክርክሩን አቅርቦ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ባለማገናዘብ አመልካች ከውል ግዴታው በላይ ብር 68,200(ስልሳ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ስለሆነም በዚህ ረገድ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማረም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ